# GBGB ፖሊሲ- የሠራተኞች ጸጥታ እና ደሕንነት

አንድ ጥቃት ሲደርስ፣ ያልተገባ ባሕሪ ሲታይ፣ በደል ሲፈጸም፣ ሆን ተብሎ የልጅ የወሲብ ጥቃት እንደተፈጸመ በሐሰት ክስ ሲቀርብ፣ ወይም አንድ ተማሪ በአስተማሪ ወይም በት/ቤት ሠራተኛ ላይ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሲከሰስ የሚከተለው አሰራር በሥራ ላይ ይውላል።

የአንድ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ንብረት ላይ በትምህርት ቤቱ ክልል ውስጥ በተማሪ ጉዳት ሲደርስ ተመሳሳይ አሰራር በሥራ ላይ ይውላል።

1. አስተማሪው ወይም ሠራተኛው በጽሑፍ ለርዕሰ መምህሩ፣ የሱፐር ኢንቴንዳንቱ ቢሮ" እና ለትምህርት ቦርዱ ያሳውቃል።

2. ርዕሰ መምህሩ አቤቱታውን እና ተጨባጭ ማስረጃውን ከተቀበለ በኋላ፣ ባለው አሰራር መሰረት ተማሪውን ከትምህርት ቤት ለሶስት ቀናት ያግደዋል።

3. ሱፐር ኢንቴንዳንቱ ተማሪው በሰው ወይ በንብረት ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ወቅት ትምህርት ለተጨማሪ ቀኖች የሚያቋርጥበት ወይም ከትምህርት ገበታው የሚባረርበት ደንብ ያመቻቻል።

4. ሱፐር ኢንቴንዳንቱ ወይም ወኪሉ ሃላፊ ክስተቱን ለዲስትሪክት አቃቤ ሕግ ወይ በአካባቢው ለሚገኘው የጉዳዩ ሕግ አስፈጻሚ ወይ የወንጀል ወይም ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች የሚፈጸሙት ኢሕጋዊ ጸረ-ማህበራዊ ተግባራት (delinquency proceedings) ክሶች ለሚመሰርተው ባለስልጣን ሪፖርት ያደርጋል።

5. የዚህ ፖሊሲ ቅጂ ለነፍስ-ወከፍ ተማሪ ተሰራጭቶ በየአንድ አንዱ ትምህርት ቤት ህንጻዎች ይለጠፋል።

የዲሲፕሊናዊ እርምጃ መረጃ አስተላለፍ

ርዕሰ-መምህሩ ወይም ወኪሉ በዲስትሪክቱ የተመዘገበ ማንኛውም ተማሪ የሚመለከት ከተማሪው ጋር ቀጥታዊ ግንኙነት ላላቸው አስተማሪዎችና አማካሪዎች በሙሉ ዲሲፕሊናዊ መረጃ ይሰጣል። እጅግ በጣም አስቸጋሪ የሆነ ጸባይ ያለው ተማሪ የተመደበለት ማንኛውም መምህር ወይ አማካሪ የተማሪውን የጸባይ መዝገብ በተመለከተ መረጃ ይሰጠዋል። ይህ መረጃ የተሰጠው ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ ለማንኛውም ሶስተኛ ሰው መረጃውን አያቀብልም።

እንዲጣጠም ተደርጎ የተዘጋጀው ጁን 16፣ 2001

ሕጋዊ ዋቢዎች፥ C.R.S. 19-3-304 (3.5),(4)
C.R.S. 22-32-109 (1)(x)
C.R.S. 22-32-110 (4)(b)(II)
C.R.S. 22-32-126
C.R.S. 22-33-106 (1)(d)

ተዛማጅ ማጣቀሻ፥ JK፣ የተማሪ ዲሲፕሊን
JKD/JKE፣ የተማሪዎች መታገድ/መባረር